የክህደት ሰራዊትና የአማኞች ምላሽ



አዘጋጅ፡- ሀቢብ ሰይድ
Email: hhabibsseid@gmail.com

<u>የክህደት ሰራዊትና የአማኞች ምላሽ</u>

وَلَا يَزَالُونَ يُقَاتِلُونَكُمْ حَتَّىٰ يَرُدُّوكُمْ عَن دِينِكُمْ إِنِ اسْتَطَاعُوا

…….. (ከሐዲዎች) ቢችሉ ከሃይማኖታችሁ እስከሚመልሳችሁ ድረስ የሚዋጉዋችሁ ከመሆን አይቦዝኑም።…… (ሱረቱል በቀራህ 2፡217)

ይህ የቁርአን አንቀጽ የእስልምና ጠላቶች በዚህ ዉጥንቅጡ በበዛበት አለም ዉስጥ ለሰዉ ልጆች ሰላማዊ መፍትሄ የያዘዉን እስልምናን ለማጥቃትና ለማጥፋት፤ አማኞቹን ከተዉሂድ (አሀዳዊ አምልኮ) ወደ ጣኦት የአምልኮ ስርአት ለመመለስ ሁሌም እንደማይተኙና የተመቻቸዉን አጋጠሚዎች ሁሉ ለመጠቀም እንደሚጥሩ ያረጋገጠ ነበር። ምንም እንኳ ምእመናንን ያልተጋደሉ፤ ከሀገራቸዉም ያላስወጡ መልካም የሆኑ ኢ-አማኞች እንደነበሩና በነዚህ አምሳያዎች ላይም በጎ መዋል፤ ጥሩ መስተንግዶና መልካም ምላሽ መስጠት እንዳለብን አላህ በቁርአኑ ቢገልጽልንም።

لَّا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَارِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ [٦٠:٨]

ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ (ከሓዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደእነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም። አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና። (ሱረቱል ሙምተሀና 60፡8)

እስልምናን ከሚወጉት ጋርም ቢሆን ወደ ሰላም ከተዘነበሉ ወደ ሰላም መዘንበልና ሰላምን ማዉረድ የምእመናን ባህሪ ነዉ። ምክኒያቱም እስልምና በራሱ የሰዉን ልጅ ዉሥጣዊና ዉጫዊ ሰላም ከመጠበቅ ዉጭ ሌላ አላማ የለዉምና!

وَإِن جَنَحُوا لِلسَّلْمِ فَاجْنَحْ لَهَا

ወደ ዕርቅም ቢያዘነብሉ ወደ እርሷ አዘንብል።..... (ሱረቱል አንፋል 8፡ 61)

በየዘመኑ የተላኩት የአላህ ነቢያትና መልእክተኞች ይዘዉ በመጡት የፈጣሪ አንድነትና ብቸኝነት/የተዉሂድ እምነት ምክኒያት አንዳቸዉም ከከሀዲያን በኩል ተቃዉሞ፤ ጥቃትና ጦርነት ሳይደርስባቸዉ ያለፉ አልነበሩም።

ኢብራሂም (ዐ.ሰ) በነብይነት የተላከባቸዉ ህዝቦችን በእጃቸዉ ከጠረቧቸዉ ጣኦታት እንዲርቁና የሁሉም ፈጣሪ የሆነዉን አላህ (ሱ.ወ) ብቻ እንዲገዙ በጠየቃቸዉ ጊዜ እጅግ በጣም ግዙፍ እሳት በማቀጣጠል በሷ ዉስጥ እንዲጣል አድርገዋል።

قَالُوا ابْنُوا لَهُ بُنْيَانًا فَأَلْقُوهُ فِي الْجَحِيمِ [٣٧:٩٧]

«ለእርሱም ግንብን ገንቡ በእሳት ነበልባል ውስጥ ጣሉትም» አሉ። (ሱረቱል ሷፋት 37፡97)

ምንም እንኳ እሳቷ በሱ ላይ ሰላማዊና የማታቃጥል ብትሆንለትም።

قُلْنَا يَا نَارُ كُونِي بَرْدًا وَسَلَامًا عَلَىٰ إِبْرَاهِيمَ [٢١:٦٩]

«እሳት ሆይ! በኢብራሂም ላይ ቀዝቃዛ፤ ሰላምም ሁኚ» አልን። (ሱረቱል አንቢያእ 21፡69)

በነፍስ ጭምር እስከመጨረሻዉ ለመታገል ለቆረጡ አማኞች የአሸናፊነት ቃል ከአለማቱ ጌታ ዘንድ ተረጋግጧልና!

وَإِنَّ جُنْدَنَا لَهُمُ الْغَالِبُونَ [٣٧:١٧٣]

ሰራዊቶቻችንም በእርግጥ አሸናፊዎቹ እነርሱ ናቸው። (ሱረቱል ሷፋት 37፡173)

በፈርኦን ዘመን የነበሩ ደጋሚዎች ነቢዩሏህ ሙሳ (ዐ.ሰ) ያመጣዉ ድግምት ሳይሆን ከአለማት ጌታ የመጣ ተአምር መሆኑን ባወቁና በፈጣሪያቸዉ በማመን ሱጁድ በወረዱ ጊዜ የፈርኦንም ምላሽ እግሮቻቸዉንና እጆቻቸዉን እንደሚቆራርጥ ፤ እንደሚሰቃቅላቸዉም መዛት ነበር።

[١٢٠] قَالُوا آمَنَّا بِرَبِّ الْعَالَمِينَ [١٢١] رَبِّ مُوسَىٰ وَأُلْقِيَ السَّحَرَةُ سَاجِدِينَ وَهَارُونَ [١٢٢] قَالَ فِرْعَوْنُ آمَنتُم بِهِ قَبْلَ أَنْ آذَنَ لَكُمْ ۖ إِنَّ هَٰذَا لَمَكْرٌ مَّكَرْتُمُوهُ فِي الْمَدِينَةِ لِتُخْرِجُوا مِنْهَا أَهْلَهَا ۖ فَسَوْفَ تَعْلَمُونَ [١٢٣] لَأُقَطِّعَنَّ أَيْدِيَكُمْ وَأَرْجُلَكُم مِّنْ خِلَافٍ ثُمَّ لَأُصَلِّبَنَّكُمْ أَجْمَعِينَ [١٢٤]

ድግምተኞቹም ሰጋጆች ኾነው ወደቁ። አሉ፦ «በዓለማት ጌታ አመንን።» «በሙሳና በሃሩን ጌታ።» ፈርዖን አለ፦ «እኔ ለእናንተ ሳልፈቅድላችሁ በፊት በእርሱ አመናችሁን ይህ በከተማይቱ ውስጥ ሰዎቿን ከእርሷ ለማውጣት በእርግጥ የተስማማችሁበት ተንኮል ነው። ወደፊትም (የሚደርስባችሁን) ታውቃላችሁ።» «እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን በማፈራረቅ በእርግጥ እቆራርጣለሁ። ከዚያም ሁላችሁንም በእርግጥ እሰቅላችኋለሁ።»

(ሱረቱል አእራፍ 7፡120-124)

እነሱም ጥፋት ተብሎ የተቆጠረባቸዉ በአላህ በማመናቸዉ ብቻ መሆኑን ለፈርኦን ምላሽ ይሰጣሉ።

وَمَا تَنقِمُ مِنَّا إِلَّا أَنْ آمَنَّا بِآيَاتِ رَبِّنَا لَمَّا جَاءَتْنَا ۚ رَبَّنَا أَفْرِغْ عَلَيْنَا صَبْرًا وَتَوَفَّنَا مُسْلِمِينَ [٧:١٢٦]

«የጌታችንም ተዓምራቶች በመጡልን ጊዜ ከማመናችን በቀር ከእኛ አትጠላም። ጌታችን ሆይ! በእኛ ላይ ትዕግስትን አፍስስ። ሙስሊሞች ኾነን ግደለን።» (ሱረቱል አእራፍ 7፡126)

ይህም አማኞች ‹‹ ጌታችን አንድ ነዉ።›› በማለታቸዉ ብቻ ከኩፋሮች ዘንድ የማጥፋት ዘመቻ እንደሚከፈትባቸዉ ማሳያ የሆነ የቀደምት ምእመናን የታሪክ ምሳሌ ነዉ።

ነቢዩሏህ ኑህ (ዐ.ሰ) ተመሳሳይ ዛቻ ከህዝባቸዉ ዘንድ ተሰንዝሮባቸዋል።

قَالُوا لَئِن لَّمْ تَنتَهِ يَا نُوحُ لَتَكُونَنَّ مِنَ الْمَرْجُومِينَ [٢٦:١١٦]

«ኑሕ ሆይ! (ከምትለው) ባትከለከል በእርግጥ ከሚወገሩት ትኾናለህ» አሉት። (ሱረቱል ሹአራእ 26፡116)

ነቢዩ ሉጥ (ዐ.ሰ) ህዝባቸዉን አጸያፊ ከሆነዉ የዝሙት ተግባር በከለከላቸዉ ጊዜ ምላሻቸዉ እሱንና ተካታዮቹን ከከተማዉ አስወጧቸዉ መባባል ነበር።

وَلُوطًا إِذْ قَالَ لِقَوْمِهِ أَتَأْتُونَ الْفَاحِشَةَ مَا سَبَقَكُم بِهَا مِنْ أَحَدٍ مِّنَ الْعَالَمِينَ [٨٠] إِنَّكُمْ لَتَأْتُونَ الرِّجَالَ شَهْوَةً مِّن دُونِ النِّسَاءِ ۚ بَلْ أَنتُمْ قَوْمٌ مُّسْرِفُونَ [٨١] وَمَا كَانَ جَوَابَ قَوْمِهِ إِلَّا أَن قَالُوا أَخْرِجُوهُم مِّن قَرْيَتِكُمْ ۖ إِنَّهُمْ أُنَاسٌ يَتَطَهَّرُونَ [٨٢]

ሉጥንም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። «አስቀያሚን ሥራ ትሠራላችሁን? በእርሷ ከዓለማት አንድም አልቀደማችሁም።» «እናንተ ከሴቶች ሌላ ወንዶችን በመከጀል በእርግጥ ትመጡባቸዋላችሁ። በእውነቱ እናንተ ወሰንን አላፊዎች ሕዝቦች ናችሁ።» የሕዝቦቹም መልስ « (ሉጥንና ተከታዮቹን) ከከተማችሁ አውጧቸው። እነሱ የሚጥራሩ ሰዎች ናቸውና» ማለት እንጂ ሌላ አልነበረም። (ሱረቱል አእራፍ 7፡80-82)

ሹዐይብ (ዐ.ሰ) የመድየን ህዝቦችን ወደ አሀዳዊ አምልኮ ጥሪ ባደረገላቸዉ ጊዜ ጥሪህን አንቀበልም ብቻ አልነበረም ያሉት። ይልቁንም እሱና ተከታዮቹ እነሱ ወዳሉበት የጣኦት አምልኮ እስካልተመለሱ ድረስ ከከተማቸዉ እንደሚያባርሯቸዉ ነበር ዛቻ የሰነዘሩባቸዉ።

قَالَ الْمَلَأُ الَّذِينَ اسْتَكْبَرُوا مِن قَوْمِهِ لَنُخْرِجَنَّكَ يَا شُعَيْبُ وَالَّذِينَ آمَنُوا مَعَكَ مِن قَرْيَتِنَا أَوْ لَتَعُودُنَّ فِي مِلَّتِنَا ۚ قَالَ أَوَلَوْ كُنَّا كَارِهِينَ [٧:٨٨]

ከሕዝቦቹ እነዚያ የኮሩት መሪዎች፡- «ሹዓይብ ሆይ! አንተንና እነዚያን ከአንተጋር ያመኑትን ከከተማችን በእርግጥ እናስወጣችኋለን፡፡ ወይም ወደ ሃይማኖታችን መመለስ አለባችሁ አሉ፡፡ የጠላንም ብንኾን? » አላቸው፡፡ (ሱረቱል አእራፍ 7፡88)

የነቢያቶች መደምደሚያ የሆኑት ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) በተላኩበት ጊዜም ከሀዲያን እሳቸዉን ለመግደል ብዙ ጥረዋል፡፡ተከታዮቻቸዉ ላይ እንግልትና ግድያ ፈጽመዋል፡፡ ከእንግልቱና ስቃዩ ፋታ ለማግኘትም ተከታዮቻቸዉ ወደ ሀበሻ ምድር ሁለት ጊዜ ተሰድተዋል፡፡ በመጨረሻም የአላህ መልእክተኛና መካ ላይ የነበሩ ባልደረቦቻቸዉ/ አስሀቦች ሀገራቸዉንና ሀብት ንብረቶቻቸዉን ጥለዉ ወደ መዲና ተሰድተዋል፡፡ ከሀዲያን ይህም አልበቃ ብሏቸዉ አማኞችን ከምድረገጽ ለማጥፋት መዲና ድረስ ጦር ሰብቀዉባቸዋል፡፡ እንዲገደሉና ከሀገራቸዉ እንዲወጡ የተደረጉበትም ‹‹ጌታችን አላህ ነዉ፡፡›› ከማለታቸዉ በስተቀር ሌላ ምንም አይነት ወንጀል እንዳልነበረባቸዉ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይገልጸዋል፡፡

الَّذِينَ أُخْرِجُوا مِن دِيَارِهِم بِغَيْرِ حَقٍّ إِلَّا أَن يَقُولُوا رَبُّنَا اللَّهُ ۗ

ለእነዚያ «ጌታችን አላህ ነው» ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት፡፡..... (ሱረቱል ሐጅ 22፡40)

ይህም የቁርአን አንቀጽ/አያ አማኞች በሀይል፤ በገንዘብም ሆነ በማንኛዉም ነገር ይቀናቀኑም አይቀናቀኑም፤ ጉልበት ይኑራቸዉም አይኑራቸዉም ለአለማቱ

ፈጣሪ ታዛዥ/ ሙስሊም በመሆናቸዉ ብቻ ኩፋሮች እነሱን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት እንደማይተኙላቸዉ ያረጋገጠ ነበር። አላህም(ሱ.ወ) የአማኞችን ታሪክ ምሳሌ ከመስጠትም በተጨማሪ ኩፋሮች እነሱን ለማጥፋት ሌት ተቀን ሳያንቀላፉና ሳይቦዝኑ ሁልጊዜ እንደሚንቀሳቀሱ ትምህርት ይሆናቸዉ ዘንድ በቀጥታ እንዲህ ያስጠነቅቃቸዋል።

وَلَا يَزَالُونَ يُقَاتِلُونَكُمْ حَتَّىٰ يَرُدُّوكُمْ عَن دِينِكُمْ إِنِ اسْتَطَاعُوا

……. (ከሐዲዎች) ቢችሉ ከሃይማኖታችሁ እስከሚመልሳችሁ ድረስ የሚዋጉዋችሁ ከመሆን አይቦዝኑም።…… (ሱረቱል በቀራህ 2፡217)

በዚህም የከሀዲያኖች ቋሚ ባህሪ ምክኒያት የሰላምና ፍትህ ምንጭ የሆነዉ መለኮታዊ መመሪያ እስልምና ይጠበቅ ዘንድ ጂሀድ ተደንግጓል። ጂሀድ እንደ አጥፊዉች እንቅስቃሴ መጠን የተወሰነ ነዉ። በአንደበት፤ በገንዘብና በሌሎች ቀላል መንገዶች መመለስ የሚቻል ይኖራል። ድንበር አልፈዉ በሚመጡ፤ አማኞችንና እምነቱን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት በሚሞክሩት ላይ ግን ፊት ለፊት በነፍስ ጭምር መታገል በግዴታነት ተደንግጓል።

كُتِبَ عَلَيْكُمُ الْقِتَالُ وَهُوَ كُرْهٌ لَّكُمْ ۖ وَعَسَىٰ أَن تَكْرَهُوا شَيْئًا وَهُوَ خَيْرٌ لَّكُمْ ۖ وَعَسَىٰ أَن تُحِبُّوا شَيْئًا وَهُوَ شَرٌّ لَّكُمْ ۗ وَاللَّهُ يَعْلَمُ وَأَنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ [٢:٢١٦]

መጋደል እርሱ ለእናንተ የተጠላ ሲሆን በእናንተ ላይ ተጻፈ። አንዳች ነገርን እርሱ ለናንተ የበለጠ ሲሆን የምትጠሉት መኾናችሁ ተረጋገጠ። አንዳችንም ነገር እርሱ ለናንተ መጥፎ ሲሆን የምትወዱት መሆናችሁ ተረጋገጠ። አላህም (የሚሻላችሁን) ያውቃል ግን እናንተ አታውቁም። (ሱረቱል በቀራህ 2፡216)

በዚህ የቁርአን አንቀጽ/አያ ላይ ምንም እንኳ ጂሀድ በዉስጡ መሞት፤ መቁሰል፤ እንዲሁም ሌሎች ከባድና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ቢኖሩበትምና በዚህም ምክኒያት በአማኞች ልብ ዉስጥ የተጠላ ቢሆንም መደንገጉን

ይገልጻል። አማኞች መጥፎ ነዉ ብለዉ የጠረጠሩት ጂሃድና ሌሎች ነገሮች ለነሱ ጥሩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያብራራል። ምክኒያቱም መታገል በድል፤ በጠላቶች ላይ የበላይነት፤ በሰላም መስፈንና በእምነት መጠበቅ የሚከተል በመሆኑ ነዉ። ይልቁንም አላህ አማኞች ጥሩ ነዉ ብለዉ ያሰቡት ከትግል መዘናጋት በጠላቶቻቸዉ የበላይነት ከመጨቆን፤ በሰይጣናዊ ስርአት ከመሰቃየት፤ ከመታገልም በላይ ዋጋ ከመክፈል ዉጭ በዉስጡ መልካም ነገር እንደሌለዉ በመግለጽ ከነሱ በላይ ለነሱ ምን እንደሚጠቅማቸዉ፤ የነገሮች መጨረሻቸዉ ምን እንደሚሆን እንደሚያዉቅና የሱን ትእዛዞች እንዲከተሉ ያሳስባል።

እነዚያ ሀገራቸዉን ጥለዉ የተሰደዱት የዚህ ኡማ ቀደምቶች ከከሀዲያን በኩል የሚደርስባቸዉን ግፍ ጥለዉ ወደ መዲና በተሰደዱበት ጊዜ በቁጥርም ትንሽ፤ በአቅምም ደካማ፤ በኢኮኖሚም ገና ያልጠነከሩ ነበሩ። ነገር ግን የጠላቶቻቸዉ ሴራና ዘመቻ የማቋያርጥ በመሆኑና ባለማቋረጡ በዚህ ትንሽ አቅማቸዉ እራሳቸዉን እንዲከላከሉ እሱም እንደሚረዳቸዉ አላህ የሚከተለዉን የቁርአን አንቀጽ አወረደ።

أُذِنَ لِلَّذِينَ يُقَاتَلُونَ بِأَنَّهُمْ ظُلِمُوا ۚ وَإِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ نَصْرِهِمْ لَقَدِيرٌ [٢٢:٣٩] الَّذِينَ أُخْرِجُوا مِن دِيَارِهِم بِغَيْرِ حَقٍّ إِلَّا أَن يَقُولُوا رَبُّنَا اللَّهُ ۗ

ለእነዚያ ለሚገደሉት (ምእመናን) እነርሱ የተበደሉ በመኾናቸዉ (መጋደል) ተፈቀደላቸዉ።።አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው። ለእነዚያ «ጌታችን አላህ ነው» ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት (ተፈቀደ)።..... (ሱረቱል ሐጅ 22፡39-40)

በዚህም የመጀመሪያዉ የበድር ጦርነት በሙስሊሞች አሸናፊነት ተጠናቀቀ።

በኸንደቅ ዘመቻ ጊዜም ከተለያየ ስፍራ የተሰበሰቡ ከሀዲያን መዲናን ሙሉ በሙሉ ከበዉ እጅግ ትንሽ ቁጥር ያላቸዉን አማኞች ላንደየና ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥፋት ሞክረዉ ነበር።

إِذْ جَاءُوكُم مِّن فَوْقِكُمْ وَمِنْ أَسْفَلَ مِنكُمْ

ከበላያችሁም ከናንተ በታችም በመጡባችሁ ጊዜ፣..... (ሱረቱል አህዛብ 33፡10)

ነገር ግን የአማኞች ምላሽ ወደኋላ መመለስ ሳይሆን እንዲህ የሚል ነበር።

وَلَمَّا رَأَى الْمُؤْمِنُونَ الْأَحْزَابَ قَالُوا هَٰذَا مَا وَعَدَنَا اللَّهُ وَرَسُولُهُ وَصَدَقَ اللَّهُ وَرَسُولُهُ ۚ وَمَا زَادَهُمْ إِلَّا إِيمَانًا وَتَسْلِيمًا [٣٣:٢٢]

አማኞቹም አሕዛብን ባዩ ጊዜ «ይህ አላህና መልክተኛው የቀጠሩን ነው። አላህና መልክተኛውም እውነትን ተናገሩ» አሉ። (ይህ) እምነትንና መታዘዝንም እንጂ ሌላን አልጨመረላቸውም። (ሱረቱል አህዛብ 33፡22)

አላህም በከሀዲያን ላይ ነፋስን እና መላኢካዎችን በመላክ እንዲሸነፉ አደረጋቸዉ፡

:

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا اذْكُرُوا نِعْمَةَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ جَاءَتْكُمْ جُنُودٌ فَأَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ رِيحًا وَجُنُودًا لَّمْ تَرَوْهَا

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ብዙ ሰራዊት በመጣችባችሁና በእነርሱ ላይ ነፋስንና ያላያችኋትን ሰራዊት በላክን ጊዜ በእናንተ ላይ (ያደረገላችሁን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ።..... (ሱረቱል አህዛብ 33፡9)

‹‹ለዘመናት የተደራጀና እጅግ የሰለጠነ በብዙ መቶ ሽዎች የሚቆጠር ሰራዊት ያላቸዉ የነፋርስና/Persia ሮማን/Rome የመሳሰሉ ግዛቶች ባሉበት፤ መላ አረቢያና አለም ለነሱ ጠላት በሆነችበት በዛን ጊዜ ለምን ራስን መከላከል/ጂሀድ ተደነገገ? ከትንሽ መቶዎች እምብዛም የዘለለ ብዛት ያልነበራቸዉ አማኞች ለምን

ትንሽ በቁጥርና በአቅም እስኪጠናከሩ ድረስ አላህ ይህን ሱራ አላዘገየዉም? ›› ለሚለዉ ጥያቄ የሚሰጠዉ መልስ የነገሩን ፍሬ ሀሳብ ያስገነዝበናል።

ምላሹም ኢ-አማኞች/ኩፋሮች እስልምናን ከስር ከስሩ ለማጥፋት የማይተኙ ከሆነ እስልምናን በዳእዋ ከማስፋፋት ጎን ለጎን በመጀመሪያና ወደ እስልምና እየገባ ያለዉን አማኝ እንዲሁም አሁን ያሉትንና ወደፊት የሚገነቡትን የአላህ ቤቶችና መድረሳዎች መጠበቅና ዋስትና ማግኘት ስላለባቸዉና አላህም ለአማኞች ረዳት ስለሆነ ነዉ።

አለበለዚያማ ኩፋሮች በሰአታት ዉስጥ ሊያጠፉት የተሰለፉለትን አማኝ መከትከት፤ ሊያቃጥሉት ፍም ያያያዙለትን መስጂድ መገንባት፤ ሊበታትኑት ሴራ የሚጎነጉኑለትን መድረሳ ማነጽ ምን ሊሰራ? ምንስ ሊፈይድ? ምንስ ሊጠቅም? ነገሩ ዉሀ ቅዳ ዉሀ መልስ ከሆነ መልፋቱ ምን ዋጋ አለዉ? ይሄ ሲባል ግን ዋስትና ካላገኘ ወደ እስልምና የሚደረገዉ ጥሪ/ዳእዋ ይቁም ማለት አይደለም። አላህ ከፈለገ ከኩፋሮችም ቢሆን ለሱ የሚታገሉ አማኞችን ሊያወጣ ይችላልና!

يُخْرِجُ الْحَيَّ مِنَ الْمَيِّتِ وَيُخْرِجُ الْمَيِّتَ مِنَ الْحَيِّ

ሕያውን ከሙት ያወጣል። ሙታንም ከሕያው ያወጣል።..... (ሱረቱል ሩም 30፡19)

በጃሚኢ ቲርሚዚይ ሀዲስ ቁጥር 2616 ሙአዝ ኢብኑ ጀበል (ረ.ዐ) በአንድ ወቅት ከረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ጉዞ ላይ በነበረበት ጊዜ የነገሩትን በተረከበት ሀዲስ ላይ ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ጂሀድን የእስልምና ሻኛዉ ነዉ ብለዉታል።

‹‹ أَلاَ أُخْبِرُكَ بِرَأْسِ الأَمْرِ كُلِّهِ وَعَمُودِهِ وَذِرْوَةِ سَنَامِهِ ›› . قُلْتُ بَلَى يَا رَسُولَ اللَّهِ . قَالَ ‹‹ رَأْسُ الأَمْرِ الإِسْلاَمُ وَعَمُودُهُ الصَّلاَةُ وَذِرْوَةُ سَنَامِهِ الْجِهَادُ››

.....‹‹ስለ ሁሉም ነገር እራሱን፤ ምሰሶዉን እና ሻኛዉን አልነግርህም ወይ?›› እኔም አልኩ‹‹እንዴታ የአላህ መልእክተኛ!›› እሳቸዉም አሉ፡

‹‹የነገሩ ሁሉ እራስ እስልምና ነዉ። ምሰሶዉ ሶላት ነዉ። ሻኛዉ ጂሀድ ነዉ፡ ፡››.....

ምክኒያቱም ቋሚ የሆነ ጠላት ያለዉ ነገር ግን መከላከያ ሰራዊት የሌለዉ ሀገር እንዴት ዋስትና አግኝቶ እንደሀገር ሊቆም ይችላል? እንዴትስ ራሱን መጠበቅ ይችላል?

የአላህ መልእክተኛና(ሰ.ዐ.ወ) አስሀቦች(ረ.ዐ) እስልምናን ለመጠበቅ ሁሌም በተጠንቀቅና በዝግጅት ነቅተዉ ይጠብቁ ነበር። ቀስቶቻቸዉን እና ሰይፎቻቸዉን ጠበቅ አድርገዉ ይዘዉ ይንቀሳቀሳሉ። በተለይም ደግሞ ከጠላት በኩል የጥቃት ስጋት በተሰማቸዉ ጊዜ እራሳቸዉን ከመቸዉም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ያዘጋጃሉ። የጠላቶቻቸዉንም እንቅስቃሴ ሌት ተቀን ይሰልላሉ። ረሱል(ሰ.ዐ.ወ) ሰላዮችን በቡድን በቡድን እያደረጉ ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ይልካሉ። የከሀዲያንን የሴራ መረብ በእንጭጩ ይበጣጥሱታል። ይህ አንደኛዉ የእለት ተእለት ጫት ማታ ስራቸዉ ነበር። ጠላቶቻቸዉም ጥቃት ከሰነዘሩባቸዉ ሙሉ በሙሉ መደምሰስ እየቻሉ ቢሆንም እንኳ እነሱም ተመጣጣኝና ድንበር ያላለፈ የአጸፋ ምላሽ ይሰጡ ነበር። አላማዉ እጆቻቸዉን እንዲሰበስቡ ማድረግ ብቻ ነበረና!

وَقَاتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ الَّذِينَ يُقَاتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوا ۚ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ [٢:١٩٠]

እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ። ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና። (ሱረቱል በቀራህ 2፡190)

አማኞች የእስልምናን ጥቃት ልክ ሰምተዉ እንዳልሰሙና አይተዉ እንዳላዩ እጆቻቸዉንና እግሮቻቸዉን አጣጥፈዉ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዉ የሚቀመጡ ከሆነ የአለማቱ ተቆጣጣሪ አላህ(ሱ.ወ) ጠንከር ያለ ወቀሳ ያቀርብባቸዋል።

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا مَا لَكُمْ إِذَا قِيلَ لَكُمُ انفِرُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ اثَّاقَلْتُمْ إِلَى الْأَرْضِ

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በአላህ መንገድ (ለመታገል) ውጡ በተባላችሁ ጊዜ ወደ ምድር የምትወዘፉት ለእናንተ ምን አላችሁ?..... (ሱረቱል ተዉባህ 9፡38)

የተሰጣቸዉን ግዴታ አለመወጣታቸዉ ከፍጥረታቱ አስገኝ ዘንድ ጠንከር ያለ ቅጣት ያስከትልባቸዋል። ምናልባትም አማኞች ፈተና በአላህ እጅ መሆኑን ዘንግተዉ ከከሀዲያን ዘንድ ስቃይ ይደርስብናል ብለዉ በመፍራት ለእስልምና መታገልን ሊተዉ ይችላሉ። ምንም እንኳ ለአላህ የሚታገሉ አማኞችን እሱ የበላይ ያደረጋቸዉና የሚያደርጋቸዉ ቢሆንም! ነገር ግን የዚች አለም አስተናባሪ የሆነዉ የሁሉ ነገር ባለቤት፤ ነገሮችን በሙሉ ሁን በሚለዉ ትእዛዛዊ ቃል ብቻ ማድረግ የሚችለዉ የብርቱ ሀይል ባለቤቱ ጌታ ማስጠንቀቂያስ እንዴት ችላ ይባል?

إِلَّا تَنفِرُوا يُعَذِّبْكُمْ عَذَابًا أَلِيمًا وَيَسْتَبْدِلْ قَوْمًا غَيْرَكُمْ وَلَا تَضُرُّوهُ شَيْئًا ۗ وَاللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ [٩:٣٩]

ለዘመቻ ባትወጡ (አላህ) አሳማሚን ቅጣት ይቀጣችኋል። ከእናንተ ሌላ የኾኑንም ሕዝቦች ይለውጣል። በምንም አትጎዱትምም። አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው። (ሱረቱል ተዉባህ 9፡39)

እስልምናን ለመጠበቅ በአንደበት፤በገንዘብና በነፍስ መታገልን/ ጂሀድ መተዉ የዚህ ኡማ የዉርደት መንስኤ ነዉ። በሱነን አቢ ዳዉድ ሐዲስ ቁጥር 3462 ኢብኑ ዑመር (ረ.ዐ) እንደተረከዉ የአላህ መልእክተኛ ጂሀድን መተዉ በሀራም ከመዘፈቅና እና ዱኒያን አለቅጥ ከማፍቀር ጋር አንድ ላይ በመጥቀስ የዚህ ኡማ ዉርደት አንዱ ምክኒያት እንደሆነ ግልጽ አድርገዋል። እነዚህንም ሶስት ነገሮች አሟልተን እስካልተመለስን ድረስም ሙሉ በሙሉ ዲን ላይ እንዳልሆንን፤ እስከምንመለስ ድረስም በዉርደታችን ላይ እንደምንቀጥል አብራርተዉልናል።

عَنِ ابْنِ عُمَرَ، قَالَ سَمِعْتُ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم يَقُولُ« إِذَا تَبَايَعْتُمْ بِالْعِينَةِ وَأَخَذْتُمْ أَذْنَابَ الْبَقَرِ وَرَضِيتُمْ بِالزَّرْعِ وَتَرَكْتُمُ الْجِهَادَ سَلَّطَ اللَّهُ عَلَيْكُمْ ذُلاًّ لاَ يَنْزِعُهُ حَتَّى تَرْجِعُوا إِلَى دِينِكُمْ »

‹‹በሪባ/አራጣ በተገበያያችሁ ጊዜ፤ የከብቶችን ጭራት በያዛችሁ/ በተከተላችሁ ጊዜ፤ እርሻን በወደዳችሁ ጊዜ እና ጂሀድን በተዋችሁ ጊዜ አላህ ዉርደትን ያከናንባችኋል። ይህንንም ዉርደት ወደ ዲናችሁ እስካልተመለሳችሁ ድረስ ከእናንተ አያነሳም።››

ጂሀድ አሚር የሚቀመጥለት፤ ቅድመ ሁኔታዎችና መስፈርቶች የሚሟሉለት፤ እንደየሁኔታዉ በተለያዩ መንገዶችና ዘዴዎች የሚተገበር፤ እንደየክብደቱና ምእመናን አቅም መጠን ከቃላት ዉርወራ እስከ ኢኮኖሚያዊ ትግል ብሎም በሕይወት ጭምር እስከመጋፈጥ የሚደርስ በጥልቅ ምርምርና እዉቀት ላይ የተመሰረተ ከጊዜ፤ ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚሄድ መለኮታዊ ተግባር ነዉ፡ ፡

አላህ(ሱ.ወ) አማኞችን ከከሀዲያን በኩል ሊቃጣባቸዉ ለሚችል ማንኛዉም ጥቃት ንቁ ሁነዉ እንዲጠብቁ ያዛል። ራስን መከላከል በእስልምና ጠላት በመጣ ቁጥር ለመመለስ የሚደረግ መሯሯጥ ላይ ሳይሆን ተዘጋጅቶ መጠበቅ ላይ መሰረት ያደረገ ነዉ። የተበታተነና ያልተዋቀረ ሀይል እስኪሰባሰብና እስኪናበብ ድረስ ጠላት በፍጥነት ጥቃቱን አስፍቶ ለዝግጅትም ፋታ ሊያሳጣዉ ቢችልስ? የተደራጀንና ጠንካራ የሆነን የአማኞች ሀይልማ ለማጥቃት መች ከጅምሩ ሀሳቡ ይመጣለትና? ለምእመናን የሚጠቅማቸዉን አዋቂ የሆነዉ አላህ(ሱ.ወ) እንዲህ ብሎ ያዛቸዋል፡-

وَأَعِدُّوا لَهُم مَّا اسْتَطَعْتُم مِّن قُوَّةٍ وَمِن رِّبَاطِ الْخَيْلِ تُرْهِبُونَ بِهِ عَدُوَّ اللَّهِ وَعَدُوَّكُمْ وَآخَرِينَ مِن دُونِهِمْ لَا تَعْلَمُونَهُمُ اللَّهُ يَعْلَمُهُمْ ۚ وَمَا تُنفِقُوا مِن شَيْءٍ فِي سَبِيلِ اللَّهِ يُوَفَّ إِلَيْكُمْ.....

ለእነሱም ከማንኛውም ኃይልና ከታጀቡ ፈረሶችም የቻላችሁትን ሁሉ በእርሱ የአላህን ጠላትና ጠላታችሁን ሌሎችንም ከእነርሱ በቀር ያሉትን የማታውቋቸውን አላህ የሚያውቃቸውን (መናፍቃን) የምታሸብሩበት ስትኾኑ አዘጋጁላቸው። ከማንኛውም ነገር በአላህ መንገድ የምትለግሱትም ምንዳው ወደናንተ በሙሉ ይሰጣል።..... (ሱረቱል አንፋል 8፡60)

በዚህ የቁርአን ኣያ ላይ ቅድመ ዝግጅት ለጥፋት የሚመጣን የከሀዲያን ሀይል ከመከላከል በተጨማሪ እኩይ ሀሳብ ባላቸዉ የሰይጣን ሰራዊቶች ዉስጥ ፍርሀት በመልቀቅ አላማቸዉ ላይ ከጅምሩ ዉሀ ይከልስባቸዋል።

ለዛም ነበር የዚህ ኡማ ቀደምቶች ጠንካራ አሚር ባለዉ፤ እጅግ ጥብቅ በሆነ መዋቅር በተሰራና ጠላት የሚርድለት በሆነ ጠንካራ የሙጃሂዶች ስብስብ እስልምናን ሲጠብቁ የቆዩት!

አስሀቦች ለጂሀድ በወጡ ጊዜ የአሰላለፋቸዉን ማማር አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይገልጸዋል።

إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الَّذِينَ يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِهِ صَفًّا كَأَنَّهُم بُنْيَانٌ مَّرْصُوصٌ [٦١:٤]

አላህ እነዚያን እነርሱ ልክ እንደ ተናሰ ግንብ የተሰለፉ ኾነው በመንገዱ (በሃይማኖቱ) የሚጋደሉትን ይወዳል። (ሱረቱል ሶፍ 61፡4)

ጂሀድ ሸሂድነትን የሚናፍቁ አማኞች ባንድ ላይ ሁነዉ እስልምናን ለመጠበቅ የሚያደርጉት የነቢያቶች ፈለግ ነዉ። አንድ ትዉልድ ለጂሀድ ለራሱ የማይሣሣና ለነፍሱ የቆረጠ መሆን ቢኖርበትም ልክ እንደ አስሀቦች እስከሚሆን ድረስ ይጠበቅ መባል የለበትም። እንደ አስሀቦቹ ያለ ትዉልድ እስከ አለም ፍጻሜ/ቶለተ ቂያማ ድረስ ሊመጣ እንደማይችል በሀዲስ ተነግሯል። ኧረ እንደዉም ከነሱ በኋላ ያሉትንም ሁለት ትዉልዶች የሚመስላቸዉ ወደ ፊት አይገኝም።

በሰሂህ ቡኻሪ ሀዲስ ቁጥር 3650ና በሰሂህ ሙስሊም ተመሳሳይነት ባለዉ ዘገባ ሀዲስ ቁጥር 2535 ኢምራን ቢን ሁሰይን (ረ.ዐ) እንደተረከዉ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል።

خَيْرُ أُمَّتِي قَرْنِي ثُمَّ الَّذِينَ يَلُونَهُمْ ثُمَّ الَّذِينَ يَلُونَهُمْ

‹‹ከኔ ተከታዮች ምርጡቹ በኔ ዘመን ያሉት ናቸዉ፤ ከዛም ቀጥሎ ያሉት፤ ከዛም ቀጥሎ ያሉት.....››

ነገር ግን ጂሀድ ለዚህ ኡማ እስከመጨረሻዉ የአለም ፍጻሜ ድረስ የተደነገገ ግዴታ ነዉ። ጂሀድ በዋነኛነት የአላህ እገዛ እንጂ በአማኞች ቁጥር፤ ብርታት፤ ጥንካሬና በመሳሰሉት ላይ ብቻ የመሰረተ አይደለም። አስሀቦች(ረ.ዐ) በሁነይን ዘመቻ ላይ በአቅማቸዉና በቁጥራቸዉ ከሀዲያንን በቀላሉ እንደሚያሸንፉ በተኩራሩ ጊዜ ድል ከአላህ መሆኑን ይረዱ ዘንድ በጠላቶች ክፉኛ ተፈትነዉ ነበር፡ ፡ ምንም እንኳ በመጨረሻ አሸናፊዎች ቢሆኑም!

ለአመታት በተሰራ የከሀዲያን ሴራና በሙስሊሙ የእዉቀት ችግር ምክኒያት ዛሬ ላይ የዲን አካል መሆኑ እስኪረሳ ድረስ የተዘነጋዉ ጂሀድ ኡማዉን ብዙ ዋጋ ማስከፈሉን ቀጥሏል። ታዲያ ይሄ ኡማ ይህን የእስልምና ሻኛ ተብሎ የተገለጸዉን ጂሀድ እርግፍ አድርጎ የተወበት ምክኒያቱ ምን ይሆን?

ከንግግራቸዉ ወህይ እንጂ ሌላ የማይወጣዉ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) የነቢያቶቻቸዉን ትእዛዝ አንቀበልም በማለታቸዉ ጥመትና ጥፋት የወደቀባቸዉ የእስራኤል ልጆች ሁኔታ በዚህም ኡማ ላይ እንደሚወድቅበት ተንብየዋል።

በጃሚኢ ቲርሚዚይ ሐዲስ ቁጥር 2641 አብደላህ ቢን አምር (ረ.ዐ) እንደተረከዉ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል።

‹‹لَيَأْتِيَنَّ عَلَى أُمَّتِي مَا أَتَى عَلَى بَنِي إِسْرَائِيلَ حَذْوَ النَّعْلِ بِالنَّعْلِ

‹‹በእስራኤል ልጆች ላይ የመጣባቸዉ በኔ ኡማ ላይም ኮቴ በኮቴ ይመጣበታል.....››

አላህም (ሱ.ወ) ከምርጦእች በኋላ በስሜቶቻቸዉ የሚነዱ ምትኮች እንደሚተኩ ሲናገር፡-

فَخَلَفَ مِن بَعْدِهِمْ خَلْفٌ أَضَاعُوا الصَّلَاةَ وَاتَّبَعُوا الشَّهَوَاتِ.....

ከእነሱም በኋላ ሶላትን ያጓደሉ (የተዉ) ፍላጎቶችንም የተከተሉ መጥፎ ምትኮች ተተኩ!..... (ሱረቱል መርየም 19፡59)

የፈጣሪ ቃል የሆነዉ ቁርአንና የአላህ መልእክተኛ ንግግር *ሀዲስ* እስኪዘነጋ ድረስ መሀይምነትና የግለሰብ ተከታይነት ባየለበት በዚህ አስገራሚ ዘመን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) እና የነዛ ብርቅየ ባልደረቦቻቸዉን ፈለግ/*ሱና* እንደታሪክ ብቻ ከንፈራችንን እየመጠጥን እንድንናደምጠዉና ከደቂቃዎች በኋላ ከናካቴዉ እርግፍ አድርገን እንድንረሳዉ ምክኒያት ሁኗል።

ግለሰቦች፤ ታላላቅ አሊሞች ቢሆኑም እንኳ እስልምናን በከፊል ሊያንጸባርቁት እንጂ ሙሉ በሙሉ ሊወክሉት አይቻላቸዉም። አንድ አሊም ምናልባትም ዐቢድና አሊም ሁኖ ሙጃሂድ ላይሆን ይችላል። ሌላዉ አሊምና ሙጃሂድ ሁኖ ዐቢድ ላይሆን ይችላል። አሊምም በራሱ በሁሉ ነገር ላይ አዋቂ መሆንም አይችልም። የሰዉ ልጅ እድሜ ከእዉቀት ጡጦ ሳይላቀቅ በፊት ያከትማል። ሁሉም ሼኾችና አሊሞች ልዩ የሆነ የመጠቁበት የየራሳቸዉ የእዉቀት ዘርፍ አላቸዉ። በዛዉም ላይ የሰዉ ልጅ ስለሆኑ ስህተት አያጣቸዉም። ኢልም/እዉቀት ፈላጊ ሰዉ ከትቂቶቹ ብቻ የፈለገዉን ነገር ማግኘት ይሳነዋል። ይሄ ማለት ግን አሊሞችን ደረጃቸዉን ማሳነስ አይደልም። ወደ አላህ ቃል ቁርአንና ወደ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) ተግባር/ሱና መዳረሻ ድልድይ መሆናቸዉ ሳይታለም የተፈታ ነዉ።

የዲነል ኢስላም/እስልምና ሀይማኖት ምሳሌ ሊሆኑና እምነታችንን በሙሉነት ልናይባቸዉ የምንችላቸዉ የፍጡራኖች ሁሉ በላጭ የሆኑት ታላቁ ሰዉ የአላህ ነቢይ ሙሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) ብቻ ናቸዉ።

لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِي رَسُولِ اللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُو اللَّهَ وَالْيَوْمَ الْآخِرَ وَذَكَرَ اللَّهَ كَثِيرًا [٣٣:٢١]

ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው፣ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አልላችሁ። (ሱረቱል አህዛብ 33፡21)

وَأَنزَلْنَا إِلَيْكَ الذِّكْرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ مَا نُزِّلَ إِلَيْهِمْ وَلَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ [١٦:٤٤]

.....ወደ አንተም ለሰዎች ወደእነሱ የተወረደውን (ፍች) ልትገልጽላቸውና ያስተነትኑም ዘንድ ቁርኣንን አወረድን። (ሱረቱል ነህል 16፡44)

እስልምናን በደመነፍሳችን በመረጥናቸዉ ጥቂት ግለሰቦች መነጽር ብቻ እንመለከዋለን ካልን የእምነቱን ከፊል ተግብረን ከፊሉን መዘንጋታችን አይቀርም። የዚህም መጨረሻዉ በዚህ አለም ዉርደትና በቀጣይ አለም የአላህ ቅጣት ይሆናል።

أَفَتُؤْمِنُونَ بِبَعْضِ الْكِتَابِ وَتَكْفُرُونَ بِبَعْضٍ ۚ فَمَا جَزَاءُ مَن يَفْعَلُ ذَٰلِكَ مِنكُمْ إِلَّا خِزْيٌ فِي الْحَيَاةِ الدُّنْيَا ۖ وَيَوْمَ الْقِيَامَةِ يُرَدُّونَ إِلَىٰ أَشَدِّ الْعَذَابِ ۗ وَمَا اللَّهُ بِغَافِلٍ عَمَّا تَعْمَلُونَ [٢:٨٥]

.....በመጽሐፉ ከፊል ታምናላችሁን? በከፊሉም ትክዳላችሁን? ከእናንተም ይህንን የሚሠራ ሰው ቅጣት በቅርቢቱ ሕይወት ውርደት እንጂ ሌላ አይደለም። በትንሣኤ ቀንም ወደ ብርቱ ቅጣት ይመለሳሉ። አላህም ከምትሠሩት ሥራ ሁሉ ዘንጊ አይደለም። (ሱረቱል በቀራህ 2፡85)

ታዲያ በዚህ ዘመን ያለ የሙስሊሞች ዉርደት ከፊል እስልምናን ከመከተል ዉጭ በምንስ ምክኒያት ሊሆን ይችላል? ለነገሩስ የነዚያ በደምና አጥንታቸዉ ዲኑን ያቆሙት የአስሀቦቹ ታሪክ ዛሬ የት አለ?

ሙስሊሞች በመስጂደል አቅሷ ዉስጥ በሚገደሉበት ዘመን! በጠራራ ጸሀይ በሚጨፈጨፉበት! ለምን ሶላት ሰገዳችሁ፤ጌታችሁን አላቃችሁ ተብለዉ በጅምላ እስር ቤት በሚታጎሩባት አለም!

አማኞች ይሄን እያዩና እየሰሙ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለዉ ተከናንበዉ ከተኙ የሙጃሂድነት እድላቸዉ ከነሱ ተቀምቶ ለሌሎች ህዝቦች ይሰጣል። ምክኒያቱም እነሱ እንጂ እስልምና የግድ የበላይ መሆን ስላለበት።

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا مَن يَرْتَدَّ مِنكُمْ عَن دِينِهِ فَسَوْفَ يَأْتِي اللَّهُ بِقَوْمٍ يُحِبُّهُمْ وَيُحِبُّونَهُ أَذِلَّةٍ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ أَعِزَّةٍ عَلَى الْكَافِرِينَ يُجَاهِدُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ وَلَا يَخَافُونَ لَوْمَةَ لَائِمٍ ۚ ذَٰلِكَ فَضْلُ اللَّهِ يُؤْتِيهِ مَن يَشَاءُ ۚ وَاللَّهُ وَاسِعٌ عَلِيمٌ [٥:٥٤]

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከእናንተ ውስጥ ከሃይማኖቱ የሚመለስ ሰው አላህ (በእነርሱ ስፍራ) የሚወዳቸውንና የሚወዱትን፣ በምእመናን ላይ ትሑቶች፣ በከሓዲዎች ላይ ኀያላን የኾኑን በአላህ መንገድ የሚታገሉን የወቃሽን ወቀሳ የማይፈሩን ሕዝቦች በእርግጥ ያመጣል። ይኸ የአላህ ችሮታ ነው፤ ለሚሻው ሰው ይሰጠዋል፤ አላህም ችሮታው ሰፊ ዐዋቂ ነው። (ሱረቱል ማኢዳህ 5:54)

የእኛ መጨረሻስ! በነፋስ! በዉሀ! በበሽታ! በጦርነትና በሌሎችም ቅጣቶች እንደተጠፉት ህዝቦች ካልሆነ በስተቀር በምድር ላይ መቀመጣችን ምን ሊፈይድ!

فَهَلْ يَنظُرُونَ إِلَّا سُنَّتَ الْأَوَّلِينَ ۚ فَلَن تَجِدَ لِسُنَّتِ اللَّهِ تَبْدِيلًا ۖ وَلَن تَجِدَ لِسُنَّتِ اللَّهِ تَحْوِيلًا [٣٥:٤٣]

.....የቀድሞዎቹን ደንብ እንጂ ይጠባበቃሉን? ለአላህ ደንብም መልለወጥን አታገኝም። ለአላህ ደንብም መዛወርን አታገኝም።

(ሱረቱል ፋጢር 35:43)

ስለዚህ ወደ ዲን መመለስ ወይስ መጥፋት!

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا كُونُوا أَنصَارَ اللَّهِ كَمَا قَالَ عِيسَى ابْنُ مَرْيَمَ لِلْحَوَارِيِّينَ مَنْ أَنصَارِي إِلَى اللَّهِ ۖ قَالَ الْحَوَارِيُّونَ نَحْنُ أَنصَارُ اللَّهِ

እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የመርየም ልጅ ዒሳ ለሐዋርያቶቹ «ወደ አላህ ረዳቴ ማነው?» እንዳለ ሐወርያቶቹም «እኛ የአላህ ረዳቶች ነን» እንዳሉት የአላህ ረዳቶች ኹኑ።..... (ሱረቱል ሶፍ 61፡14)

ወሰላሙ ዓለይኩም

መጽሐፍቶች ፡- Telegram ፡ http://t.me/habibamharicbooks

አጫጭር መጣጥፎችና የድምጽና ምስል ዳእዋዎች፡-

፡ - Telegram:-

Page http://t.me/hhabibsseid

group http://t.me/habibislamic

የድምጽና ምስል ዳእዋዎች፡-

Youtube:https://youtube.com/channel/UC68a1aUodvASDgKNyqziPOg

ሰኔ 2014

…….. (ከሐዲዎች) ቢችሉ ከሃይማኖታችሁ እስከሚመልሳችሁ ድረስ የሚዋጉዋችሁ ከመሆን አይቦዝኑም።..... **(ሱረቱል በቀራህ 2፡217)**

በአላህ መንገድና ከወንዶች ከሴቶችና ከልጆችም የኾኑትን ደካሞች እነዚያን፡- «ጌታችን ሆይ! ከዚች ባለቤቶችዋ በዳይ ከኾኑት ከተማ አውጣን ከአንተም ዘንድ ለእኛ አሳዳሪን አድርግልን ከአንተ ዘንድም ለእኛ ረዳትን አድርግልን» የሚሉትን (ለማዳን) የማትጋደሉት ለእናንተ ምን አላችሁ **(ሱረቱል ኒሳእ 4፡75)**